

# እርስዎ እነሱን ሊጠብቋቸው ይችላሉ

## በጀርመን ውስጥ ውጤታማ የሆነ
## የመራቢያ አካላት ግርዛት መከላከል

የሚመከር ድርጊት በ
**SAIDA International e.V.**



# ይዘት፡


የዚህ በራሪ ጽሁፍ ዓላማ ምንድን ነው? 2

እንኳን ደህና መጡ 3

የመግቢያ መረጃ 5

በጀርመን ውስጥ ያለ ሁኔታ 9

ውጤታማ የሆነ መከላከል 11

ማማከር እና እገዛ 13

ማህተም 14




## አደጋን ይለዩ፣ በሃላፊነት ይጓዙ እና ልጃገረዶችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ይጠብቁ

www.saida.de





# የዚህ በራሪ ጽሁፍ ዓላማ ምንድን ነው?

**ውድ ባለሙያተኞች እና የሚመለከታችሁ ሰዎች፦**

ልጆች -- በተለይ በቤተሰቡ ውስጥ ጥቃት ሲደርስባቸው ጊዜ፣ የማህበረሰቡ እና የመንግስት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። በጀርመን ውስጥ፣ ብዙ ሺህ ልጃገረዶች ልዩ የሆነ የጥቃት፦ የመራቢያ አካላት ግርዛት የመጋለጥ አደጋ ያጋጥማቸዋል።
የተጠቁት ሴቶች እና ልጃገረዶች ብዙ ጊዜ በእኛ ውስጥ ሳይታወቅባቸው ይኖራሉ። እምብዛም መቼም ቢሆን እርዳታ አይጠይቁም አይተን እንዳላየን መሆን አንችልም።
የመጡበት አገር ያላቸው ባህል የሚያሳየው ይሄ ተግባር ምን ያህል ቀጣይነት እንዳለው ነው። ሆኖም ግን፣ እንደዚሁም ቡርኪናፋሶ ውስጥ ከሚገኘው SAIDA ልጃገረዶች ጥበቃ መርሀግብር የተማርነው፣ ውጤታማ የሆነ የመከላከል መርሀግብር የሚቻል እንደሆነ ነው። ለምዕተ ዓመታት ሲፈጸም ስለነበረው ጥቃት የዳራ ታሪክ ብዙ ሰዎች ባወቁ ቁጥር እና በጀርመን ውስጥ ስላለው ሁኔታ ካወቁ፣ የመከላከሉ ዕድል ከፍተኛ ነው። ስለዚህ፣ የመከላከል ተጽእኖ ለመፍጠር የሁሉም ሰው ትኩረት ያስፈልጋል።
በማህበራዊ፣ ሕክምና እና የትምህርት ባለሙያ የሆኑ ክህሎት ያላቸው ሠራተኞች እንደዚሁም ፖሊስ እና የፍትህ ዘርፍ ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ።

በዚህ በራሪ ጽሁፍ ድጋፍ ለማቅረብ እንፈልጋለን ስለዚህ ሊፈጠር የሚችለውን አደጋ በትክክል መገምገም እንችላለን እና ልጃገረዶቹ ያለምንም ስጋት እንዲያድጉ ማስቀጠል እንችላለን። ምክንያት፦ **እርስዎ** እነሱን **ሊጠብቋቸው** ይችላሉ

**ከአክብሮት ጋር፣ ሲሞን ሽዋርዝ**
ዋና አስተዳዳሪ ጸሐፊ

## FGM በተጨባጭ ምን ማለት ነው?

የእንግሊዘኛው ኤፍጂኤም (FGM) ምሕፃረ ቃል ለሴቶች የመራቢያ አካላት ግርዛት (Female Genital Mutilation) ማለት ነው። ስያሜው ለመጀመሪያ ጊዜ የወጣው 1990 ላይ በአለም አቀፍ ኮሚቴ ጎጂ የሆኑ ባህላዊ ተግባራት [Harmful Traditional Practices (IAC)]ነበር።
የአለም አቀፍ ጤና ድርጅት [World Health Organisation (WHO)] በእነሱ የቢሮ ቋንቋ አጠቃቀም ውስጥ የኤፍጂኤምን (FGM) ቃል ይጠቀማሉ። በተጨማሪ “የሴት ግርዛት” ወይም “የሴት መራቢያ አካላት ግርዛት“ የሚለውም ቃል ብዙ ጊዜ ያገለግላል።
የ IAC ዓባልት በ29 የአፍሪካ ሀገሮች፣ አውሮፓ እና አውስትራሊያ ውስጥ ከሚደረጉ ኢኒሼቲቮች ጋር እነዚህን ቃላቶች፣ ይሄ ጥቃት ላይ የሚደረገውን ትግል ይጎዳል በማለት፣ የሚያንቋሽሹ በመሆናቸው ተቀባይነት እንዳያገኙ አድርገዋል።
SAIDA የ IAC’ን ለአለም አቀፍ ማህበረሰብ የመራቢያ አካላት ግርዛት የሚለውን ቃል እንዲጠቀሙ የሚለውን ጥሪን ይደግፋል።



## ድ አንባቢ፣

እኛ ግልጽ እና ሁሉን ቻይ ማህበረሰብ ነን። ከሌላ አገር ባህል ወደ ጀርመን የሚመጡ ሰዎች በዚህ ረገድ ባህላቸውን እና እምነታቸውን የማራመድ ዕድል ይኖራቸዋል። ሆኖም ግን፣ የሌሎች መሰረታዊ መብቶች እስካልተጣሱ ድረስ ይተገበራል። ሰብዓዊ መብቶች በባህል ለድርድር አይቀርቡም። የልጃገረድ መራቢያ አካላቶች ግርዛት አደገኛ የሆነ የሰውነት ጉዳት ነው እና ከፍተኛ የሆነ የስነ አምዕሮ ጉዳት ያስከትላል። ፆታ ላይ-ያነጣጠረ የከፋ አድሎ እና ጥቃት ነው።

ከተጠቂዎቹ ጋር ሊገናኙ የሚችሉ፣ የባለሙያ ዘርፎች፣ ሁኔታው ላይ ሊሰማቸው እንደሚችል ግልጽ ነው። የሕክምና ባለሙያዎች እና ማህበራዊ ሠራተኞች በቂ የሆኑ ስልጠናዎች ማግኘት ይኖርባቸዋል። ለስደቶች የጋራ መኖሪያ፣ መዋዕለ ሕፃናት፣ ትምህርት ቤቶች እና የሐኪም ቀዶ ጥገናዎች ላይ መመልከት እና ማዳመጥ አስፈላጊ ስለሆነ።

የመራቢያ አካላት ግርዛት ተግባርን የዷለዷሉ የወንዶች የሚመራ ስርዓት መዋቅሮች መሰረት ናቸው። እነዚህን መዋቅሮችን መናድ በጣም አድካሚ ሂደት ነው። መረጃ፣ ትምህርት እና ማበረታታት ቁልፍ ሚና ይጫወታሉ። ከዚህ አደገኛ ተግባር በመካከላችን የሚኖሩ ሴቶችን መጠበቅ እና የተጠቁትን ሴቶች አመቺ የሆነ ድጋፍ መስጠት የእኛ አላማ መሆን አለበት። አደጋ ላይ ለተጋለጡ ልጃገረዶች ጠንካራ፣ በራሳቸው የሚተማመኑ እና ልበ ሙሉ እና ራሳቸውን የቻሉ ሴቶች እንዲሆኑ አስተዋጽዖ ማድረግ አለብን።

SAIDA International e.V. የተባለው ማህበር ለዓመታት ያህል መከላከል ላይ በቁርጠኝነት ሲሰራ ነበር እና አደጋ ውስጥ ላሉ እና ለተጠቁ ልጃገረዶች እና ሴቶች የማማከር አገልግሎት ያቀርባል። ለዚህ ወሳኝ ሥራ አጋሮቼ ስኬቱ እንደሚያስቀጥሉ እመኛለሁኝ።



**ፕሮፌሰር ዶ/ር ቶማስ ፋቢያን**
በሌፕዚንግ ውስጥ የወጣቶች፣ ማህበራዊ ጉዳዮች፣
እና የጤና እና ትምህርት ቤቶች ከንቲባ እና ሃላፊ።

## ክቡራን እና ክቡራት፣



የመራቢያ አካላት ግርዛት በአንዳንድ አጋራት ውስጥ የሴቶችን ባህሪ ለመቆጣጠር እያገለገለ ይገኛል። ያልተገረዙ ሴቶች "ልክ እንደ ቆሸሹ" እና "ለጋብቻ እንደማይሆኑ" ተደርገው ይታያሉ። በስደት የተነሳ፣ ችግሩ በሕዝብ ሕይወት ውስጥ በጣም ጎልቶ እየታየ እየመጣ ነው። ይሄ አይነቱ ጥቃት ካለበት አገር የመጡ ቁጥራቸው እየጨመረ የመጡ ሴቶች እና ልጆች አሁን በሳክሶኒ ውስጥ ይኖራሉ። በስደት ውስጥ፣ አደጋ ላይ የመሆናቸው ዕድል አነስተኛ አይደለም እና የተጠቁ ሴቶች ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። የመራቢያ አካላት ግርዛትን መከላከል እና ይሄ ዓይነቱ ጥቃት ላይ መረጃ ማግኘት ለእኛ ከፍተኛ የሆነ ፈተና ይፈጥርብናል።

2015 መጀመሪያ አካባቢ ጀምሮ ይሄ ዓይነት ጉዳይ ላይ የግዛቱ ከተማ ድሬስደን ዝግጅቱ ሲያቀርብ ነበር። 2016 ላይ፣ የመራቢያ አካላት ግርዛት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የተደረገው አውደ ጥናት ልክ እንደ SAIDA International e.V የመሳሰሉ የትብብር አጋሮች ጋር በመተባበር ነበር። ቅርጸቱ ተፈጥሮ ነበር እና ከዚያ ጊዜ ጀምሮ የግዛቱ ከተማ ውስጥ ሕክምና፣ ሕግ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እያንዳንዱ ዓመት ላይ ሲከናወን ነበር። በባለሙያዎች የተደረገው ተከታታይ ውይይት ወደ ተቆርቋሪነት እንዲኖር አስችሏል፣ እና ፍሬ ያላቸው የሚተገበሩ ዕቅዶች ተዘጋጅተዋል።

ለልጃገረዶች እና ወጣት ሴቶች የብቃት እና ትብብር ማዕከል፣ (sowieso e.V.)፣ SAIDA አለም አቀፍ e.V.፣ Akifra e.V., Medea e.V. እንደዚሁም የሳክሶን የግዛቱ ማህበራዊ ጉዳዮች እና የደንበኞች ጥበቃ ሚኒስቴር፣ የግዛቱ እኩልነት እና ውህደት ሚኒስቴር፣ የሳክሶኒ የክልሉ ቢሮ፣ እኩል ዕድል መኮንን ዕቃ-ነክ ያልሆነ፣ የገንዘብ እና የማደራጀት አቅም ጋር ድጋፍ ይሰጣሉ። ለዚህ ሥራ ምስጋናችንን ለማቅረብ እንፈልጋለን!

ይሄ በራሪ ጽሁፍ ይሄንን አስቸጋሪ አርዕስት መቋቋም ላይ ጠቃሚ ምክር እንደሚያቀርብሎት ተስፋ እናደርጋለን እና ስላሳዩን ዝንባሌ እናመሰግኖታለን።



**ዶ/ር አሌክሳንድራ-ካትሪን ስታኒስሎው-ከሚና**
በድሬስደን ከተማ ግዛት ውስጥ ለሴቶች እና ለወንዶች
እኩል የሆኑ ዕድሎች



# የመግቢያ መረጃ

**የአለም አገራት ማህበረሰብ የሴቶችን መራቢያ አካላት ግርዛትን የሰብዓዊ መብት ጥሰትን በአለም አቀፍ ደረጃ ሕገወጥ እንዲሆን አድርጓል እና ብዙ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ እንዲታገድ አድርገዋል። ሆኖም ግን፣ በየቀኑ 8000 ልጃገረዶች ይገረዛሉ።**

## ዓለም አቀፍ ስርጭት

ይህ በእንዲህ እንዳለ፣ የመራቢያ አካላት ግርዛት የሚገኙባቸው ብዙ አገራት የወንጀለኛ መቀጫ ሕግ አውጥተዋል።

ሆኖም ግን፣ በየዓመቱ ቢያንስ 3 ሚሊዩን የሚሆኑ ልጃገረዶች የዚህ ጉዳይ ተጠቂ ናቸው።
200 ሚሊዮን የሚሆኑ ልጃገረዶች እና ሴቶች ከዚህ አደገኛ ገፊት ጋር አብረው ይኖራሉ። በአለም አቀፍ ደረጃ ይህ ማለት እያንዳንዷ 20ኛ ሴት ተጠቂ ማለት ነው።

አንዳንድ አገራት ውስጥ፣ ልክ እንደ ግብጽ፣ ጊኒ፣ እና ሶማሊያ የመሳሰሉ፣ አብዛኛዎቹ የሴት ሕዝብ ቁጥር ውስጥ ይጠቃሉ።
አንዳንድ አገራት ውስጥ ተግባሩ የተለያዩ የብሔር ቡድኖች ላይ በከፍተኛ ደረጃ ይከናወናል።

## ዓላማው


መራቢያ አካላት ግርዛት ዓላማ የሴቶችን ወሲባዊነት ለመቆጣጠር ነው እና ይሄ ዓይነት የከፋ ጥቃት በመጠቀም ሴቶችን ታዛዥ ማድረግ ነው። ይሄ ተግባር የሚፈጽሙ ማህበረሰቦች ውስጥ ሴቶች እንደ ንብረት ነው የሚቆጠሩት እና ልዩ በሆነ ሁኔታ መድሎ ይፈጸምባቸዋል።

የተግባሩ ደጋፊዎች ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ግፊት አሳድረዋል። አንድ ቤተሰብ ልጃገረዶቻቸውን ሳይገረዙ የሚያቆዩ ከሆኑ፣ ልጃገረዶቹ ልክ እንደ "የቆሸሹ" እና ሴተኛ አዳሪዎች ዝቅ ተደርገው ይታያሉ። ማንም ሰው ከእነሱ ምግብ አይወስድም እና ለጋብቻ የማይመቹ ተደርገው ይቆጠራሉ። የመላው ቤተሰብ ክብር ከልጃገረዶቻቸው የወሲብ ባህሪ ጋር ይገናኛል።

**መራቢያ አካላት ግርዛት የልጃገረዶችን የወሲብ ባህሪ ለመቆጣጠር የታለመ ነው።**
**ያልተገረዙ ልጃገረዶች እና ቤተሰቦቻቸው ይሰደባሉ፣ ስማቸው ይጠፋል እና ማስፈራሪያ ይደርስባቸዋል።**

# የመራቢያ አካላት ግርዛት ስርጭት

ዕድሚያቸው 15 እስከ 49 የሆኑ ልጃገረዶች እና ሴቶች ላይ




- ከ 80 % በላይ
- 51 እስከ 80%
- 26 እስከ 50%
- 10 እስከ 25%
- ከ 10 % በታች

www.saida.de 2014

**ማብራሪያ፦** ኮከብ ከተደረገባቸው (*) አገራት በስተቀር፣ የመቶኛ ዋጋዎቹ የተወሰዱት ከ UNICEF ሪፖርት "Female Genital Mutilation/Cutting February 2018" የተወሰዱ ናቸው። ምንጮች፦ DHS፣ MICS፣ SHHS፣ Unicef፣ USAID፣ Wadi

# ተግባር

የአለም አቀፍ የጤና ድርጅት (WHO)፣ ለሕክምና ያልሆነ ዓላማ ውጫዊ የመራቢያ አካላት ክፍሎች ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል ከተወገዱ ወይም ከተጎዱ፣ ሁሉንም ዓይነት ተግባራት እና እንደ የሴቶች የመራቢያ አካላት ግርዛት በማለት ይፈርጃዋል፡፡ አራት ዓይነቶች አሉ፦

**ቂንጥር መቁረጥ (Clitoridectomy) (ዓይነት I)**
የልጃገረዶቹ የሚታየው የቂንጥር ክፍል በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ይቆረጣል፡፡

**ከንፈሮቹን መቁረጥ (Excision) (ዓይነት II)**
ውስጣዊው ከንፈር (inner labia) እና አንዳንዴ ውጫዊው ከንፈር (outer labia) ብዙ ጊዜ በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ይወገዳሉ፡፡ በግምት ወደ 80 በመቶ የሚጠጉ ተጠቂዎች ዓይነት I እና II ይደርስባቸዋል፡፡

**መስፋት እና ማስወገድ (Infibulation) (ዓይነት III)**
ወደ 15% የሚሆኑ ልጃገረዶች ላይ፣ ቂንጥር እና የብልቱ ውስጣዊ እና ውጫዊ ከንፈር ይቆራጣሉ እና ትንሽ የመሽኛ እና የወር አበባ መውጫ ብቻ በመተው ብልቱ እንዲሰፋ ይደረጋል፡፡
ጠበሳው የመጀመሪያ ወሲባዊ ግንኙነት ሊፈጸም ሲል የተሰፋው ይፈታል **(የተሰፋውን መፍታት (Defibulation))፡፡**
ልጅ ከተወለደ በኋላ፣ ቁስሉ በተደጋጋሚ በማጥበቅ ይሰፋል፡፡ **(ዳግመኛ መስፋት (Refibulation))**.

የአለም ጤና ድርጅት (WHO) **ዓይነት IV** ፧ላይ የተለያዩ እንዳሉ መዝግቧል፣ እነዚህም ቂንጥሩን፣ ውጫዊ የብልት ክፍሉን እና ብልቱን ማቃጠል፣ መፋቅ፣ መብሳት፣ መበየድ ናቸው፡፡

ድርጊቱ ከቦታ ወደ ቦታ፣ ልክ እንደ ብሔሩ ዓይነት፣ እና በአካባቢው ባለው ልማድ መሰረት ይወሰናል፡፡

# ሁኔታዎች

የጥቃቱ ልዩ ገጽታ በጣም ከፍተኛ የሆነ መጥፎ የንጽህና ሁናቴዎች መፈጠር እና ማደንዘዣ እና የሕመም መቀነሻ መድሐኒት አለመኖር ነው፡፡ በአጠቃላይ ግርዛት የሚፈጽሙ ሰዎች የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ቢላዋ፣ የተጠረቡ ድንጋዮች እና ምላጮች ናቸው፡፡ መድማቱን ለማቆም አመድ እና አሸዋ ይጠቀማሉ፡፡

ቁጥራቸው እየጨመሩ ያሉ የጤና ጥበቃ ባለሙያዎች አሁን ሀብታም ለሆኑ ቤተሰቦች ንጽህናውን በጠበቀ መልኩ ድርጊቱን ለማከናወን ተስማምተዋል፡፡ ይሄ ለግብጽ ጅቡቲ ወይም ሶማሊያ በተለየ መልኩ ይሰራል፡፡


# ጥቃቱ የሚያስከትላቸው ነገሮች

ለተጠቂዎቹ ጥቃቱ የከፋ፣ ብዙ ጊዜ ሕይወታቸውን ሙሉ ተጽእኖዎችን ያሳድራል፦


**እጅግ የከፉ የአካል ገፊቶች** ለምሳሌ፣ ድንጋጤ የሚያስከትል እና ሞት ሊያስከትል የሚችል ከፍተኛ የሆነ ሕመም እና የማያቋርጥ ደም መፍሰስ ናቸው፡፡ ሌሎች ተደጋጋሚ ገፊቶች ቴታነስ፣ ሽንት መስመር መያዝ እና ማበጥ ናቸው፡፡ ጥቃቱ በሚፈጸምበት ሰዓት መቆንጠጥ፣ መምታት እና እጅና እግር ጠፍሮ ማሰር አንዳንዴ የአጥንት መሰበር ሊያስከትል ይችላል፡፡

**የረጅም-ጊዜ አካል ላይ የሚከሰቱ ገፊቶች** ለምሳሌ የነርቭ መጎዳት፣ እጥዎች እና መምገል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የሽንት መተላለፊያ ትቦ፣ የማህጸን እና መራቢያ እንቁላሎች መካን የሚያደርግ ኢንፌክሽን፡፡ ሽንት መሽኛ መስመር እና አንጀት እንደዚሁም ሊጎዱ ይችላሉ፣ በተደጋጋሚ የሚከሰተው ነገር ፊኛ የመቆጣጠር ችግር ናቸው፡፡
ብዙ ጊዜ ከወሰባዊ ግንኙነቶች፣ የወር አበባ፣ እርግዝና እና ልጅ መውለድ ጋር የሚያያዙ ችግሮች ናቸው፡፡


## የተለያዩ የመራቢያ አካላት ግርዛት ዓይነቶች



**ዓይነት I**
የቂንጥር መቁረጥ (Clitoridectomy)



**ዓይነት II**
የብልቱን ከንፈር መቁረጥ (Excision)



**ዓይነት III**
መስፋት እና ማስወገድ (Infibulation)



**ዓይነት IV**
የተለያዩ ድርጊቶች

**የስነ አምዕሮ ተጽእኖዎች** በድብርት፣ የባህሪ መዛባት፣ የፍራቻ ምላሾች እና የወሲብ መዛባት ናቸው፡፡
ጥቃቱ እና የሞት ፍራቻው ተሞክሮ በጣም ብዙ ጊዜ የከፋ የስሜት ቁስል ያስከትላሉ፡፡ ብዙ ጊዜ የተጠቁት ግንኙነት ላይ እምነት የማጣት እና ግንኙነት የመፍጠር ችግር አቅም ያለማግኘት ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ ተጽእኖዎቹን አፍኖ መያዝ፣ ተስፋ መቁረጥ እና ማህበራዊ ግፊቱ ተግባሩ ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋል፡፡

## አደጋ ላይ የተጋለጡ ዕድሜዎች

ልጃገረዶች ከሕፃናንነታቸው እስከ አዋቂ ሰብ እስከሚሆኑ ድረስ አደጋ ውስጥ ናቸው፡፡ አብዛኛዎቹ በልጅነት ዕድሚያቸው ግርዛት ያጋጥማቸዋል፡፡ ሆኖም ግን፣ አንዳንድ አገራት ወስጥ አዲስ በወጣው የወንጀለኛ ሕግ የተነሳ የዕድሜው ደረጃ ከፍ ብሏል፡፡

# በጀርመን ውስጥ ያለ ሁኔታ

በፌደራል የቤተሰብ ጉዳዮች ሚኒስቴር 2017 ላይ ባደረገው ጥናት መሰረት፣ ወደ 47,000 የሚጠጉ ልጃገረዶች እና ሴቶች ከመራቢያ አካላት ግርዛት የመጠቃት አደጋ ውስጥ ወይም አስቀድመው የተጠቁ ናቸው። አሁን ባለው የሕዝብ ቁጥር የተነሳ፣ 2019 ላይ ከ 81,000 ገደማ ያህል የተጠቁ እና አደጋ ውስጥ ይኖራሉ ብለን እንገምታለን። ይሄ ሁኔታ ላይ ማህበረሰቡ በሚገባ ሁኔታ ስራውን እንዲሰራ ከፍተኛ የሆነ መሰናክል ነው።

## እርምጃ መውሰድ ያለብን ለምንድን ነው?

የመራቢያ አካላት ግርዛት መቁረጥ መሰረታዊ የሆኑ መብቶችን መጣስ እንደሆነ ይቆጠራል እና አደጋው ስር የሰደደ ከመሆኑ የተነሳ ግዛቱ የመጠበቅ ግዴታውን መወጣት አለበት። የሰው ክብር፣ ሕይወት እና የአካል ክብር መሰረታዊ መብቶች ተጥሰዋል።

የመራቢያ አካላት ግርዛት ለተጠቂው ሊቀለበስ የማይችሉ ጠባሳዎችን የሚያመጣ የከፋ ጥቃት ያስከትላል። ስለዚህ፣ በአስተማማኝ ሁኔታ ሊከሰት የሚችለውን አደጋ ለመከላከል ትክክለኛ እና ወጥ የሆነ እርምጃ ነው - አንድ ብቻ ዕድል አለ!

## ሕጋዊ ቦታ

ከ 2013 ጀምሮ ልዩ የሆነ የወንጀል ጥቃት የመራቢያ አካላት ግርዛትን "አንድን ሴት ልጅ ውጫዊ መራቢያ አካላትን የሚገርዝ ማንኛውም ዓይነት ሰው ድርጊቱን ከፈጸመ ከአንድ ዓመት ያላነሰ የእስር ቅጣት እንደሚያስከትል" በመጥቀስ ጥቃቱን ሲከታተል ነበር" (ክፍል 226a ጀርመን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ)። በተተመው የወንጀለኛ ስታስቲክስ መሰረት፣ 2017 ዓመት መጨረሻ ላይ በጀርመን ውስጥ በአንቀጽ 226a የጀርመን ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሰረት ምንም ዓይነት የሕግ ክሶች እንዳልቀረቡ ወይም በወላጆች ላይ ምንም ክስ እንዳልነበሩ ያመላክታል። የዚህ ምክንያት የወንጀል ጥሰት ድርጊቱ በድብቅ ስለሚፈጸም፣ ማስረጃው ከውጭ ከሚገኙ ሰዎች ተደብቆ ይገኛል እና የተጎዱት ልጃገረዶች ቤተሰቦቻቸውን ሸክም ላለማሸከም ዝምታን ስለሚመርጡ ነው።

ዋናው ችግር የሕክምና ሚስጥር ቃል ኪዳን ነው፣ ምክንያቱም ግርዛቱ የሚገኝ ከሆነ ለባለስልጣናቶች ጉዳዩን የማሳወቅ ግዴታ ያለመኖሩ ምክንያት ነው ልክ ፈረንሳይ ውስጥ እንዳለው ሁኔታ። የሆነ ጥቃት ተፈጽሟል ብለው የሚጠራጠሩ ከሆኑ ሐኪሞች የወጣቶችን ዋስትና ቢሮ ለማሳወቅ ማንኛውም ነገር የማድረግ መብት አላቸው።

እንደዚሁም የተጠቃው ግለሰብ የሚታይበት፣ አንዳንድ ፌደራል ግዛቶች ላይ የሚያስገድዱ የሕክምና ምርመራዎች አሉ።

ከአገር ውጪ የሚደረጉ ጥቃቶችን ለመከላከል፣ ልዩ የሆኑ ጉዳቶች ላይ ወላጆች ወደመጡበት አገር ልጆቻቸውን እንዳይወስዱ የሚያስችላቸው ፍርድ ቤቶች መብት አላቸው።

i

SAIDA ለባለስልጣናት ሪፖርት የማድረግ ግዴታ እና ለሁሉም ልጆች በመላው አገር ውስጥ አስገዳጅ የህክምና ምርመራዎች እንዲደረጉ እንዲያስገድዱ ጥሪውን ያቀርባል።



# በጀርመን ውስጥ የተጠቁ ልጃገረዶች እና ሴቶች – ግምት 2018/2019

| አገር | የመጡበት አገር ስርጭት | በጀርመን ውስጥ የሚገኙ ልጃገረዶች እና ሴቶች | ከእነዚህ ልጃገረዶች ውስጥ 18 ዓመት በታች የሆኑ | ከእነዚህ ሴቶች ውስጥ 18 ዓመት በታች የሆኑ | በአደጋ ውስጥ የሚገኙ ልጃገረዶች | የተጠቁ ሴቶች | በአጠቃላይ አደጋ ውስጥ ያሉ እና የተጠቁ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ግብጽ | 87% | 10,570 | 2,855 | 7,715 | 2,484 | 6,712 | 9,196 |
| ኢትዮጵያ (Ethiopia) | 65% | 9,095 | 1,980 | 7,115 | 1,287 | 4,625 | 5,912 |
| ቤኒን | 9% | 840 | 215 | 625 | 19 | 56 | 76 |
| ቡርኪና ፋሶ | 76% | 585 | 130 | 455 | 99 | 346 | 445 |
| አይቮሪ ኮስት | 37% | 2,185 | 440 | 1,745 | 163 | 646 | 808 |
| ጅቡቲ | 93% | 75 | 10 | 65 | 9 | 60 | 70 |
| ኤርትራ | 83% | 23,005 | 6,230 | 16,775 | 5,171 | 13,923 | 19,094 |
| ጋምቢያ | 75% | 1,905 | 410 | 1,495 | 308 | 1,121 | 1,429 |
| ጋና (Ghana) | 4% | 16,890 | 3,890 | 13,000 | 156 | 520 | 676 |
| ጊኒ | 97% | 3,490 | 940 | 2,550 | 912 | 2,474 | 3,385 |
| ጊኒ-ቢሳዋ | 45% | 310 | 85 | 205 | 225 | 92 | 317 |
| ኢንዶኔዥያ* | 49% | 11,370 | 540 | 10,835 | 265 | 5,309 | 5,574 |
| ኢራቅ** | 8% | 103,050 | 40,835 | 62,215 | 3,267 | 4,977 | 8,244 |
| የመን | 19% | 2,345 | 670 | 1,675 | 127 | 318 | 446 |
| ካሜሮን (Cameroon) | 1% | 10,655 | 1,490 | 9,165 | 15 | 92 | 107 |
| ኬኒያ | 21% | 8,320 | 830 | 7,490 | 174 | 1,573 | 1,747 |
| ላይቤሪያ | 44% | 290 | 55 | 235 | 24 | 103 | 128 |
| ማሊ | 83% | 455 | 130 | 325 | 108 | 270 | 378 |
| ማውሪታኒያ | 67% | 170 | 30 | 140 | 20 | 94 | 114 |
| ኒጀር | 2% | 240 | 70 | 170 | 1 | 3 | 5 |
| ናይጄሪያ | 18% | 28,095 | 9,420 | 18,680 | 1,696 | 3,362 | 5,058 |
| ሴኔጋል | 23% | 1,390 | 215 | 1,175 | 49 | 270 | 320 |
| ሴራሊዮን | 86% | 1,260 | 360 | 900 | 310 | 774 | 1,084 |
| ሶማሊያ | 98% | 15,250 | 5,230 | 10,020 | 5,125 | 9,820 | 14,945 |
| ሱዳን*** | 87% | 1,860 | 545 | 1,315 | 474 | 1,144 | 1,618 |
| ታንዛንያ | 10% | 875 | 95 | 780 | 10 | 78 | 88 |
| ቶጎ | 5% | 5,005 | 920 | 4,085 | 46 | 204 | 250 |
| ቻድ | 38% | 140 | 50 | 85 | 19 | 32 | 51 |
| ኡጋንዳ**** | 1% | 1,340 | 175 | 1,165 | 2 | 12 | 13 |
| መካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ | 24 % | 50 | 10 | 40 | 2 | 10 | 12 |
| **አጠቃላይ** | | **261,110** | **78,855** | **182,240** | **22,566** | **59,021** | **81,587** |

**ምንጮች፡-** የፌደራል ስታትስቲክስ ቢሮ፣ ከውጭ የመጡ ሴቶች ሕዝብ በዜግነታቸው እና በዕድሜያቸው መሰረት 31.12.2018 ላይ; የመጡበት አገር ላይ ስላለው ስርጭት መረጃው የተወሰደው ከ UNICEF "የሴት ልጅ የመራቢያ አካላት ግርዛት/መቁረጥ" ከሚለው ኦክቶበር 2018 የወጣው ሪፖርት እና "የኢንዶኔዥያ የሴት ልጅ መራቢያ አካላት ግርዛት ስታስቲካል መግለጫ" 2019፣ መረጃው የተዋቀረው በ SAIDA International e.V., ከኤፕሪል 2019 ጀምሮ ነው። አጠቃላይ የአሰራር ሂደቱን እና ዘዴዎቹን ላይ ገለፃ www.saida.de/genitalverstümmelung/situation-in-europa

* ስለ ኢንዶኔዥያ መሰረታዊ የጤና ምርምር የዳሰሳ ጥናት መሰረት (RISKESDAS) 2013፣ ** ስለ ኢራቅ ያለው መረጃ በሰሜን ኢራቅ የሚገኘ ግዛት የሚመለከት ነው (ራሱን የቻለ ግዛት የሆነው የኩሪዲስታን ነው)፣ *** ስለ ሱዳን ያለው መረጃ በተጨማሪ የደቡብ ሱዳንን መረጃ ያካትታል፣ **** የተለዩ ጉዳዩችን በተመለከተ

# ውጤታማ የሆነ መከላከል

## የባለሙያዎች ፈተና

የፌደራል የቤተሰብ ጉዳዮች መምሪያ የመራቢያ አካላት ግርዛት "ያለምንም ጥርጥር የልጆች ዋስትና ላይ ከፍተኛ አደጋ እንደሚያስከትል" እና "የሚመለከተው የሕዝብ የወጣቶች ዋስትና ጠባቂ ክፍል እና ፍርድ ቤቶች ከዚህ አደጋ ልጃገረዶችን መከላከል መቻላቸውን ለማረጋገጥ በጋራ እንዲሰሩ ጥሪ እንደቀረበላቸው" ያስቀምጣል።

ሆኖም ግን ይሄ ዓይነት በልጃገረዶች ላይ የሚፈጸም የልጆች ጥቃት በጣም የተለየ በመሆኑ የተነሳ ከሌሎች ዓይነት ጥቃቶች የመከላከያ መንገድ ጽንሰ ሐሳቦች በቀላሉ እዚህ ላይ ሊተገበሩ አይችሉም። ስለዚህ፣ ባለሙያዎች ልዩ የሆነ ፈተና ያጋጥማቸዋል።

## አደጋውን መገምገም

ልጃገረዶችን መጠበቅ ላይ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ሰዎች አደጋን እንዴት እንደሚለዩ እና አደጋውን እንደሚገመግሙ ማወቅ አለባቸው።

ለልጃገረዶች ላይ ሊደርስ የሚችለው አደጋ **የሚመረኮዘው**

- የመጡበት አገር ውስጥ የመራቢያ ግርዛት መኖር እና
- የሴት ዘመዶች አቋም ላይ ነው።

አደጋው **የሚከተሉት ላይ አይመረኮዝም**

- የወንጀለኛ ተጠያቂነት ግንዛቤ መኖር፣
- የችግሩን ጥልቀት እና የሚያስከትላቸውን ጠንቆች ላይ ያለው ዕውቀት
- የትምህርት ደረጃ እና ማህበረሰባዊ ከባቢ ወይም
- የሴቶች ዕድሜ መጠን።

አብዛኛዎቹ በተግባሩ ተጋላጭ የሆኑት ልጃገረዶች የሚገኙት በአፍላ የልጅነት ዕድሜ እና በ 15 ዓመት ዕድሜ መካከል ነው። ሆኖም ግን፣ የአደጋው ዕድሜ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለያየ ነው፣ በተለይ ስደት ላይ። ይሄ ማለት ዕድሜያቸው የገፉ ሴቶች ጥበቃ ሊደረግላቸው ይችላል ማለት ነው።

አደጋውን ማመላከት ላይ፣ እባክዎን ሁሉንም ሕጋዊ አማራጮች ይተግብሩ። ከወላጆች ጋር የሚደረጉ ውይይቶች በቂ እንዳልሆኑ ያስታውሱ። ሁሉን አቀፍ የመመዘኛ ስብስብ ሁልጊዜ ያስፈልጋል። ምክንያቱ የመራቢያ አካላት ግርዛት አቻ የሌለው ጥቃት ዓይነት ስለሆነ፣ ጥበቃ ሊደረግበት የሚችልበት ዕድል አንድ ብቻ ነው።

## ወደ መጡበት አገር ጉዞ በሚያደርጉበት ሰዓት አደጋ የሚደርስ ከሆነ ጥበቃ ማድረግ

አንድ የስደተኛ ዳራ ያላት ልጃገረድ ቤተሰቡ ወደመጡበት አገር ብቻዋን ወይም ከቤተሰቦችዎ ጋር ጉዞ የምታደርግ ከሆነ፣ ይሄ ሊከሰት እንደሚችል አደጋ ይቆጠራል።

በሚመለከተው አገር ውስጥ ያለው ሁኔታ በሚቀርበው ግምገማ ላይ ወሳኝ የሆኑ ነገሮች እና ባለስልጣናት ጀርመን ውስጥ ሆነው የአካባቢው ቤተሰብ ላይ መረጃ ማግኘት የማይችሉበት ደረጃ ከተደረሰ ናቸው።

የወጣቶች ዋስትና ቢሮ የሚኖሩበትን ቦታ ለመወሰን የሚያስችለውን የመገደብ መብት በመጠቀም ሕጋዊ ጥበቃ በማድረግ ከአገር ውጪ ሊፈጸም የሚችል ጥቃትን መከላከል ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።



## BGH የልጆችን የሰብዓዊ ክብር እና የአካል ክብር ጥበቃን ከፍተኛ የሆነ ቅድሚያ ይሰጣል።

የፌደራል ፍርድ ቤት ውሳኔ (BGH) ከ 15.12.2004፣ XII ZB 166/03 ኦንላይን በ፦ juris.bundesgerichtshof.de

ባለፉት ዓመታት ውስጥ በቤተሰብ ፍርድቤት የተወሰኑ ውሳኔዎች በዚህ መሰረት የሚከተሉት ነገሮች ይጋራሉ፦

- የጣልቃ ገብነት እርማጃ የተወሰደው አደጋ ውስጥ ያለ አገር ላይ የሚደረግ ጉዞ ላይ የተመሰረተ ነበር።
- የጥቃቱ ግልጽ ዕቅድ ለወላጆች በሃላፊነት አልተሰጠም።
- እውነተኛው የአደጋ ምዘና ሁልጊዜ በሚመለከተው አገር ውስጥ ያለውን ሁኔታ በመገምገም ነበር። በምናብ ደረጃ ክልል የሚያክል ሽፋን ከፍተኛ የሆነ የአደጋ ደረጃ ያስከትላል።
- የመራቢያ አካላት ግርዛት ልጆች በምንም ዓይነት ሊቋቋሙት በማይችሉት ሊቀለበሱ የማይችሉ ጠንቆችን የሚያስከትል የከፋ ጥቃት በመባል ሊተነተን ይችላል። ስለዚህ ክልከላ ሊደረገበት ይገባል።
- የሕፃንዎ ልጅ ሕይወት እና የአካል ክብር መብት የተነሳ የወላጆቹ እና የልጆቹ ሊሆን የሚችል የመጡበትን አገር የመጎብኘት መብቶችን መቀልበስ።

## በጀርመን ውስጥ ሊከሰት ከሚችል አደጋ ጥበቃ

አንድ ታዳጊ ሕፃን በጀርመን ውስጥ ወይም በሌላ የአውሮፓ ሀገራት ውስጥ ልትገረዝ ትችላለች የሚል ማንኛውም ዓይነት ጥርጣሬ ካለ፣ የወጣቶች ዋስትና ቢሮዎች የሚከተሉትን እርምጃዎችን እንዲወስዱ እንመክራለ፡

- ስለ ጥቃቱ የወንጀል ተጠያቂነት ለቤተሰቦቹ ወዲያውኑ ያነጋግሩ። ጥቃቱን ከሚፈጽም ሰው ጋር ትብብር ማድረግ ተመሳሳይ የወንጀለኛነት ጥቃት እንደሚያስከትል ያሳውቋቸው፣ ይሄ ከላይ የተጠቀሱት ጥቃቶች ላይም ይመለከታል።
- ምንም እንኳን ቤተሰቡ ድርጊቱን እንቃወማለን ብለው የሚገዙቱ ቢሆንም፣ ሁልጊዜ የመቆጣጠሪያ መሳሪያ ይፍጠሩ። መደበኛ የሆነ የሕክምና ምርመራዎችን ያዘጋጁ። ጥርጣሬ ያለ ከሆነ፣ ከቤተሰብ ፍርድ ቤት የእርስዎ ባለስልጣናት ላይ የሕክምና እንክብካቤ ዝውውር እንዲኖር ማመልከት።

# እገዛ እና የማማከር አገልግሎት

ማንኛውም ዓይነት ጥያቄዎች ያለዎት ከሆነ፣ እባክዎን እኛን ለማግኘት በማንኛውም ሰዓት ላይ ነፃነት ይሰማዎት፦

**SAIDA ከመራቢያ አካላት ግርዛት ለተጠቁ ልጃገረዶች እና ሴቶች የማማከሪያ ማዕከል**
**ስልክ: +49 (0)341 247 46 69**
**ሞባይል ስልክ፦ +49 (0)1590 166 77 63**
**ኢሜይል፦ beratung@saida.de**

ከማማከር አገልግሎት ተጨማሪ፣ ለባለሙያዎች አውደ ጥናቶችን እና የስልጠና ትምህርቶችን እናቀርባለን። የ SAIDA የብቃት ማዕከል ከቅዱስ ጆርጅ (St. Georg) ክሊኒክ ጋር በመተባበር ለሕክምና ድጋፍ ማዕከላዊ ጀርመን ውስጥ ባለብዙ ዘርፍ የመገናኛ ማዕከል ነው።

በእርስዎ አካባቢ የሚገኙ የወጣቶች ዋስትና ቢሮዎች፣ የልጆች እና ወጣቶች ድንገተኛ አገልግሎቶች እና የማማከር ቢሮዎች የመገኛ አድራሻ በየነመረብ ላይ ተዘርዝረዋል።
ሴቶች ላይ የሚደርስ ጥቃት ብሔራዊ ስልክ መቀበያ አገልግሎት ሃያ አራት ሰዓት ያለምንም ክፍያ በዚህ ስልክ ቁጥር ላይ ይገኛል ስልክ 08000 116 016።

**በጣም አስቸኳይ የሆነ አደገኛ የሆነ ነገር ከተፈጠረ የድንገተኛ አገልግሎቶች ቁጥርን በ 110 ላይ ይደውሉ።**





## እባክዎን ተጠቂዎቹን መጠበቅ ላይ ያግዙን!

## የእርዳታ መቀበያ ሒሳብ ቁጥር

**በ Ethikbank**

**IBAN DE61 8309 4495 0003 0283 13**

ለ SAIDA የሚደረጉ የገንዘብ ድጎማዎች በእርግጥ ከታክስ ነፃ ናቸው።
የእኛ ገቢዎች እናወጪዎች ላይ ያሉት ሁሉም ዝርዝሮች ኦንላይን እዚህ ላይ ተጠቅሰዋል saida.de/transparenz.


## እትም።

**አሳታሚ** SAIDA International e.V.
Käthe-Kollwitz-Str. 1
04109 Leipzig
ኢሜይል፦ info@saida.de

**አርታዒዎች** ሲሞን ሽዋርዝ፣ ጃን ሆልትሜር፣ ካትጃ ኖቫክ

**ስዕሎች** የቅጂ መብት ሲሞን ሽዋርዝ (ከገጽ. 3 እና 4 በስተቀር)

**አቋም** 2ኛ የተሻሻለው እትም ከ 2019; የመጀመሪያ እትም ከ 2016

**ምዝገባ** በ SAIDA ቢሮ ውስጥ፣ በደብዳቤ እና ያውርዱት በ፦ saida.de/IhrSchutzbistDu


www.saida.de

**SAIDA International e. V.** ከ 2010 ጀምሮ በታዳጊ አገራት ውስጥ የሴቶች እና የልጃገረዶችን መብቶች ወጥ በሆነ መልኩ የቅስቀሳ ስራ ሲሰራ ነበር። ከፆታ-ተኮር ጥቃት እና ጭቆናን ለማርገብ አካባቢያዊ እገዛ እንሰጣለን። ለሴቶች ጥበቃ፣ ትምህርት እና ጤና ውጤታማ የሆነ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ በማህበረሰቦች ውስጥ ዘላቂ የሆነ የተሻሻለ የኑሮ ሕይወት ላይ አስተዋጽዖ እናደርጋለን።

ለተጨማሪ መረጃ ወደዚህ ይሂዱ **www.saida.de** ።

saidainternational saida_info saida_international SAIDA International e.V.


**የመገኛ አድራሻ**
SAIDA International e.V.
Landsberger Str. 7
04157 Leipzig

**የመገኛ አድራሻ**
ሲሞን ሸዋርዝ

**ስልክ**
+49 (0)341 247 46 69

**ኢሜይል**
info@saida.de
www.saida.de



የዚህ ብሮሸር እትም የነበረው

gefördert durch
die Landeshauptstadt
Dresden

Dresden.